ግንቦት 2004 May 2012 የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

ቅጽ 2 ቁጥር 3
Volume2 Issue 3

# ዜና

# የፌዴራል መንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

## Public Procurement & Property Administration Agency

## News Letter

*በውስጥ ገፆች*

*በሙስናና....................1*

*በመንግስት ንብረት......1*

*ለፌደራል..................2.*

*ድረ—ገገጽ.................3*

*በአዲሱ.....................4*

*For All Public..........5*

*አላማዎች................6*
*( objectives ).*
*Pictorial news.........7*
*ዘመናዊ...............8*

በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ለውጥ
ትግበራ ዕቅድ ዝግጅትና ህዝብ ግንኙነት
ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ


የመልዕክት ሳ..ቁ 1905 / 1037
ስልክ ቁጥር .....011 123 43 86
ድረ -ገጽ www.ppa.gov.et
ስድስት ኪሎ የካቲት 12 አደባባይ


ዋና አዘጋጅ
ሲሳይ ሳህሌ
ሪፖርተር ሲሳይ ሳህሌ
ዲዛይንና የጽ/ት ስራ
ሲሳይ ሳህሌ
ተባባሪ
ድብረወረቅ መላኩ
ፎቶግራፍ
ብርሀኑና ምናሴ
ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር

## በሙስናና በሥነ ምግባር መርሆዎች ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሥነ-ምግባር ልዩ ባህርያትና የሙስና ወንጀል መከላከያ ስልቶች ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለኤጀንሲው ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሚያዚያ 19/2004 ዓ.ም በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አዳራሽ ስልጠና ሰጠ፡፡

የእለቱ ክብር እንግዳ የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተር አቶ ጀንሴ ገደፋ የስልጠናውን ዋና አላማ በመክፈቻው ሥነ-ሥርኣት ላይ እንደገለፁት ኤጀንሲው በአዋጅ የተሰጡትን ሃላፊነቶች በይበልጥ ውቴታማ በሆነ መንገድ እንዲወጣ የሚያደርግ የሥ-ነምግባር መመሪያ አዘጋጅቶ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ የተሰጠ መሆኑን አስታውሰው የመመሪያውን አስፈላጊነትና አፈፃፀም እንዲሁም የአሰራር ሥርአትና ሙስናን መከላከል በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ በገለፃና በውይይት የተሻለ ግንዛቤ ለመውሰድ እንዲቻል ስልጠናው የተዘጋጀ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አቶ ጀንሴ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የግዥ አፈፃፀም ላይ የሚታዩትን የሙስና መንገዶች ለመዝጋትና ህግና ሥርአትን ተከትሎ ግዥው እንዲከናወን ለማድረግ የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፍ ሰነዶች በማውጣት፣የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት፣ስልጠናና የምክር አገልግሎት በመስጠት እንዲሁም የግዥና ንብረት የአፈፃፀም ምርመራ በማድረግና በተከሰቱት ችግሮች ላይ እርምት እንዲውሰድ በማድረግ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርግ ኤጀንሲ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የኤጀንሲው የሥነ-ምግባር መኮንን አቶ ተስፋዬ መንገሻ በበኩላቸው የኤጀንሲው የሥነ-ምግባር መመሪያ ቅርፅና ይዘት፣ስለ ሥነ-ምግባርና ሙያ ምንነት፣ሀብት ማሳወቅና የሀብት ማስመዝገቢያ ቅፅን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በሙስና መከላከል ዙሪያ ከፍተኛ አማካሪ የሆኑት አቶ ተስፋዬ በቀለ በበኩላቸው የሙስና ልዩ ባህርያት ፣አይነቶች መገለጫዎች፣ የሚያስከትላቸው ጉዳቶችና መከላከያ ስልቶች ላይ ሰፋ ያለ ትምህርታዊ ማባራሪያና ገለፃ አድርገዋል፡፡

በቀረበው ገለፃ ላይ ከተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው በአቶ ተስፋዬ እና በአቶ በኩረፅዮን ከሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በመጡ ባለሙያዎች ለጥያቄዎቹ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በመጨረሻም ም/ዳይሬክተሩ አቶ ጀንሴ ገደፋ በመዝጊያው ሥነ-ሥርአት ላይ ኤጀንሲው የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓቱን እንዲገነዘቡ የማድረግ ሃላፊነት እንዳለበት በማስገንዘብ መላው የኤጀንሲ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ሥነ-ምግባር የተላበሰ ስራ በመስራት ያለውን የሀገሪቱን ልማት እንቅስቃሴ ለማገዝና የተሻለ ውጤት ለማምጣት ቁርጠኛ ዜጋ መሆን እንደሚገባ አሳስበው ከሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የመጡትን አሰልጣኞች አመስግነው የእለቱ ስልጠና ከቀኑ 11፡20 ሰዓት ተጠናቋል፡፡

## በመንግስት ንብረት አሰተዳደር ዙሪያ ለመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ኃላፊዎች ስልጠና ተሰጠ

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት ንብረት አስተዳደር ዙሪያ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለባለ በጀት መ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ሚያዚያ 15/2004ዓ.ም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አዳራሽ ስልጠና ሰጠ፡፡

የእለቱ የክብር እንግዳ አቶ ፀጋዬ አበበ የስልጠናውን ዋና አላማ በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ እንደገለጹት፣የመንግስት ንብረት አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ አፈጻጸም እንዲኖረው ለማድረግና መንግስት ከሚያስፈጽማቸው የልማት አጀንዳዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የስራ



ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን አቅም በማጎልበት፤በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የደንበኞች ፍላጎትን ለማርካት በሁሉም ዘርፍ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀ አፈጻጸም ፣ግልጽና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ፀጋዬ የመንግስት ንብረት አስተዳደር በአዋጁ ፣ በመመሪያውና በማንዋሎቹ መሰረት በሚፈለገው ደረጃ ባለመሰራቱ የሚፈለገው ውጤት በአጥጋቢ ሁኔታ አለመገኘቱን ከመግለጻቸውም ባሻገር በፌደራል መ/ቤቶች ያለው የንብረት አስተዳደር ስራ ተገቢ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን በተደረገው ልዩ ልዩ የክትትል ዘዴ መገንዘብ መቻሉን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም የንብረት አስተዳደር መረጃ አያያዝና የሪፖርት ልውውጥ ወደ ዘመናዊ የኤሌክትሮኒክስ አሰራር ለማሸጋገር ጥናት እየተደረገ መሆኑን ገልጸው መንግስት ያለውን ሀብት ማወቅ እንዲችል በእያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤቶች የሚገኝ እያንዳንዱ ቋሚ ንብረት አይነቱ፣ብዘቱ እና የዋጋ ግምቱ ታውቆ እንዲመዘገብና በአመታዊ የመንግስት ሂሳብ ሪፖርት እንዲጠቃለል የማድረጉ ስራ ከሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠበቅ ትልቅ ተግባር መሆኑን አስታውቀው ሰልጣኞች ወደ እየስራ ቦታቸው በሚመለሱበት ጊዜ የተዘረጋውን የመንግስት ንብረት አስተዳደር ሥርዓት በመ/ቤታቸው በትክክል ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን አሳስበዋል።

አቶ ተስፋዬ ብርሃኑ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ምክትል ዳይሬክተር በበኩላቸው በስቶክ አስተዳደር ማንዋል ላይ የተጠቀሱትን ስቶክ የመለየትና ስያሜ የመስጠት ፣ስቶክን መቀበል፣ወጪ ማድረግና ማደል፣የስቶክ መዛጋብትና ሂሳብ አሰራር ፣ ቆጠራ ፣ ቁጥጥርና ክምችትን እንዲሁም የመንግስት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል ላይ የተገለፁትን ፣የመንግስት ንብረት አስተዳደር መርሆዎች የቋሚ ንብረት አጠቃላይ ቆጠራ ፣ዋጋ ግመታ ፣የሂሳብ አመዘጋገብ ፣ማስወገድ ፣ቁጥጥርና ቆጠራ ላይ ያተኮረ ሰፋ ያለ ገለጻና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በመጨረሻም በመንግስት ግዝና ንብረት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ፀጋዬ አበበ አወያይነት አጠቃላይ ውይይት ተደርጎ ከተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎችና አስተያቶች ተነስተው ለጥያቄዎቹ ምላሽ ከተሰጣቸው በኂላ የእለቱ ስልጠና ከቀኑ 11:40 ላይ ተጠናቋል።

ለአንድ ቀን በቆየው በመንግስት ንብረት አሰተዳደር ዙሪያ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ላይ ከ170 በላይ የባለበጀት መ/ቤቶች ዳይሬክተሮችና ሌሎች ኃላፊዎች ተሳታፊ ሆነዋል።

## ለፌደራል መንግስት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ስልጠና ተሰጠ

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 በመንግስት ግዥ አፈፃፀምና በአዲሱ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ለውጦች ያተኮረ ከጥር 14-17/2004ዓ.ም ለፌደራል መንግስት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና ለተለያዩ ዩኒቨርስቲ የግዥ፣የንብረት፣የፋይናንስና የኦዲት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት

የመሰብሰቢያ አዳራሽ የመጀመሪያው ዙር ስልጠና ሰጠ፡፡

በኤጀንሲው የግዥና ንብረት ጥናትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች የሆኑት አቶ ትዕግስት ደበበ፣አቶ ዳዊት ከይሶ፣ወ/ት ትዕግስት በርታ፣ወ/ሮ ከድጃ ኑሩ እና የግዥና ንብረት ኦዲትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ባለሙያ የሆኑት አቶ አወቀ አበራ ስልጠናውን የሚሰጡ ሲሆን የስልጠናው ዋና አላማ የመንግስት ግዥን አጠቃላይ ገፅታ፣የመንግስት ግዥ ማለት ምን እንደሆነ፣የግዥ ማዕቀፍ በኢትዮጵያ፣ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አላማዎችና፣ዋና ዋና ነጥቦች ፣የመደበኛ ጨረታ ሰነድ ዋና ዋና ነጥቦችን በተመለከተና በአጠቃላይ ስለ መንግስት ግዥ አጠቃላይ ገፅታና በአዲሱ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ላይ የተካተቱ ለውጦችን ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና ለተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

አሰልጣኞቹ በግዥ ዑደት ዙሪያ ስለማቀድ፣ስለመምረጥ፣ውል ስለመዋዋል፣ስለ ውል አስተዳደር፣ዕቃን
ስለማከማቸት፣ስለማሰራጨት፣ንብረት ስለ ማስወገድና የግዥ አፈፃፀምና ግምገማ ላይ ወቅታዊ ምሳሌዎችን በመስጠትና ነባራዊ ሁኔታዎችን በማስረዳት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪም የግዥ እቅድና ለምን እንደሚያስፈልግ፣በግዥ እቅድ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች፣የግዥ እቅድ ማጠቃለያ ሃሳቦች፣የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር አዘገጃጀት፣የፍላጎት መግለጫ አጻጻፍና መግቢያ፣የፍላጎት መግለጫ አይነቶች፣የስራ ዝርዝር ማጣቀሻ (ቢጋር) ምንነትና አዘገጃጀት፣እንዲሁም ሌሎች ርዕሶች ላይ ገለፃ አድርገዋል ፡፡

በቀረበው ገለፃና ማብራሪያ ላይ ስለ ቅድሚያ ክፍያ፣አነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች፣ግዥአፅዳቂ እና ጨረታ ኮሚቴ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ከተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው ለጥያቄዎቹ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ለ4ቀናት በሚቆየው በመንግስት ግዥ አፈፃፀምና በአዲሱ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ለውጦች ያተኮረ ስልጠና ላይ ከ 150 በላይ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና የተለያዩ ዩኒቨርስቲ ባለሙያዎች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## በአዲሱ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅና መመሪያ ላይ ስልጠና ሰጠ

የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 በመንግስት ግዥ አፈፃፀምና በአዲሱ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ለውጦች ላይ ያተኮረ ከጥር 21-24/2004ዓ.ም ለፌደራል መንግስት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና ለተለያዩ ዩኒቨርስቲ የግዥ፣የንብረት፣የፋይናንስና የኦዲት ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሁለተኛውን ዙር ስልጠና ሰጠ፡፡

በኤጀንሲው የግዥ አፈፃፀምና የንብረት አወጋገድ አቤቱታ ማጣራት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ መኩሪያ ክፍሌና የዳይሬክቶሬቱ ባለሙያ አቶ ቢተውልኝ አየሁ፣ የግዥና ንብረት ጥናትና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ባለሙያዎች የሆኑት አቶ አብራር መንጋና ታደሰ ከበደ፣ እና የግዥና ንብረት ኦዲትና ክትትል ዳይሬክቶሬት ባለሙያ የሆኑት አቶ ታደለ ነጋሽ ስልጠናውን የሚሰጡ ሲሆን የስልጠናው ዋና አላማ የግዥና ንብረት አስተዳደር ተግባራት መዋሃድ፣ የተጫራቾች አቤቱታ የሚያይ ቦርድ መቋቋሙ፣በፌደራል የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ባለሙያዎችና ሀላፊዎች ሚና መለየቱ፣ለአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ልዩ አስተያየት መፈቀዱ፣ግዥ የሚፈፅምና ንብረት የሚያስወግድ ድርጅት መቋቋሙ ፣በአጠቃላይ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ አዋጅ ቁጥር 649/2001 አላማዎችን በተመለከተና ስለ መንግስት ግዥ አጠቃላይ ገፅታና በአዲሱ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ላይ የተካተቱ ለውጦችን ለፌደራል መንግስት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና ለተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ መሆኑን አሰልጣኞቹ አስታውቀዋል፡፡

አሰልጣኞቹ የመንግስት ግዥ ከግል ግዥ ስለሚለይበት ዋና ዋና ይዘቶች በፋይናንስ አስተዳደር ያለ ልዩነት ዙሪያ፣ስለአቅራቢዎች በሚኖር አመለካከት ዙሪያ ፣ስለ ትኩረትና ግልፅነት ልዩነት፣የዋና አላማና ፖሊሲ ልዩነት ፣የሚና እና ከአቅራቢዎች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ላይ ያለ ልዩነትን በተመለከተ ወቅታዊ ምሳሌዎችን በመስጠትና ነባራዊ ሁኔታዎችን በማስረዳት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪም የግዥ እቅድ ለምን እንደሚያስፈልግ፣በግዥ እቅድ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች፣የግዥ እቅድ ማጠቃለያ ሃሳቦች፣የፍላጎት መግለጫ ዝርዝር አዘገጃጀት፣የፍላጎት መግለጫ አጻጻፍና መግቢያ፣የፍላጎት መግለጫ አይነቶች፣የስራ ዝርዝር ማጣቀሻ (ቢ.ጋር) ምንነትና አዘገጃጀት፣እንዲሁም ሌሎች ርዕሶች ላይ ገለፃ አድርገዋል ፡፡

በቀረበው ገለፃና ማብራሪያ ላይ ስለ ውል አስተዳደር፣ስለ ልዩ አስተያትና አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ ስለ ትክክለኛ ጥራትና ዋጋ፣የጨረታ ሰነድ በማን መዘጋጀት እንዳለበት፣ስለ ግዥ አፅዳቂ እና ጨረታ ኮሚቴ እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ከተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ተነስተው ለጥያቄዎቹ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ለ4ቀናት በሚቆየው በመንግስት ግዥ አፈፃፀምና በአዲሱ ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ለውጦች ያተኮረ ስልጠና ላይ ከ 175 በላይ የፌደራል መንግስት ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቶችና የተለያዩ ዩኒቨርስቲ ባለሙያዎች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## ለመንግስት ግዥ ድረ-ገፅ ተጠቃሚዎች በሙሉ

**የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተለያዩ ሰነዶችን በአዲስ መልክ አወጣ**

በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአለማቀፍ የግዢ አማካሪ ባለሙያ የሆኑት Mr.Mirsolav Alilovic አማካኝነት ከአዲሱ የግዥ ህግ ጋር ተጣምረውና ተሻሽለው ነባርና አዳዲስ ሰነዶች የተዘጋጁ በመሆናቸው ሰነዶቹን በኤጀንሲው ድረ ገፅ ላይ ስለምታገኙአቸው ተጠቃሚዎች ድረ ገፁን በመክፈት ሰነዶቹን እንድትጠቀሙባቸው እንጋብዛለን ፡፡

### ሰነዶቹም

- የተሸሻሉ 8 መደበኛ የጨረታ ሰነዶች፡
- የተሻሻለ የግዥ አፈፃፀም ማኑዋል፤
- የተሸሻለ የግዥ ስልጠና ሞጁል፤
- 15 በአዲስ መልክ የተዘጋጁ የተለያዩ ሰነዶች፤
- የማዕቀፍ ግዥ መደበኛ ጨረታ ሰነድ ታትሞ የተሰራጨ፤ መሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

## For all Public Procurement Website users

International procurement consultant Mr.Miroslav Alilovic has prepared new, harmonized and improved documents based on the new Proclamation 649/2009 for public procurement and property administration Agency, Therefore, the Agency would like to remind the users of the website **ppa.gov.et** to open and use the **new**, **harmonized** and **improved** documents from the **website.**

### A. Previous documents that are harmonized and Improved by

## The new Proclamation 649/2009 rules are:-

1. Revised SBDs for Goods for: a) NCB; b) ICB. pages 193
2. Revised SBDs for Proc. of Non-Consultancy Services for: a) NCB; b) ICB. pages 202
3. Revised SBDs for Proc. of Consultancy Services for: a) NCB; b) ICB pages 234
4. Revised SBDs for Works for: a) NCB; b) ICB. pages 300
5. Revised SBDs for Proc. of Pharm. and Medical Equipment a) NCB; b) ICB pages210
6. Revised SBDs for Proc. of Information Systems (IS) for: a) NCB; b) ICB. pages 374
7. Revised SBDs for Proc. of Books and Journals for: a) NCB; b) ICB pages 191
8. Revised SBDs for Prequalification for: a) NCB; b) ICB pages 44
9. Revised existing Public Procurement Manual pages 249
10. Revised existing Public Procurement Training Module pages –

## B. Recently (Newly) Prepared documents are:-

1. Standard Bid Evaluation Report Forms pages 11
2. Standard Bid Opening Forms pages 12
3. Guideline for Procurement of Security Items pages 12
4. SBDs for Procurement of Goods and Related Services fully customized to meet requirements of Framework Agreements. a) NCB; b) ICB pages 219
5. SBDs for Procurement of Non-Consultancy Services customized to meet requirements of Framework Agreements. a) NCB; b) ICB 234
6. Manual on the Use of Framework Agreements pages 32
7. Defined the List of Common User items. pages 16
8. Procurement Audit Manual and Audit Checklist pages 85
9. *Manual on Procurement Appeal Management / Complaint Review procedure* pages *42*
10. *Defined system for price indexing and adjustment and prepared Guidance on Contract Price Adjustment.* pages *4*
11. Mapped capacity building and training needs pages 33
12. Proposed design of Public Procurement Management Information System and its incorporation within IFMIS. pages 45
13. Proposed Procurement reporting templates and performance benchmarking indicators and their inclusion into new IFMIS pages 6
14. Drafted Guideline for Public Private Partnership (PPP). pages 16
15. Drafted Schedule of Requirement for the Feasibility Study on e-GP implementation pages

ዘመናዊ የመንግስት
ግዥና ንብረት
አስተዳደር ስርዓት
በመዘርጋት
የመፈጸፀምና
የማስፈፀም አቅማችንን
እናጎለብታለን !!!